ምነው በኢሕአፓ ላይ ዘመቻው ተጧጠፈ ?

ክፍል 3

" ካልጠየቁ ኣያውቁ

ካላወቁ ኣይነቁ"

" እሳቱ ቢዳፈን የጠፋ መሰሏቸው

የራሳቸው ውሸት መልሶ ኣነቃቸው ።"

በኢሕአፓ ላይ ጸያፉ ዘመቻ እስካሁን ጋብ አላለም ፤ አልቆመም ። የዚህ ዋናው ምንጭወያኔ ቢሆንም በሕዝብ ማጥፋት ወንጀል የተጨማለቁትም ንስሓ በመግባት ፈንታ ቀደም ሲያጠፉት ሞክረው ያቃታቸውን እሳት አሁንም ሊዘምቱበትና ሊያጠፉት ተነስተዋል ማለት ይቻላል ።

አንደኛው ራዲዮ ይዞ ነጋ ጠባ ድርጅቱን የሚዘልፈው አሰላ ሳለ ተማሪዎች የሚወዱትን የታሪክ አስተማሪ ያስገደለ ነው ።

ሌላው የአራጁ መላኩ ተፈራ ቀኝ እጅ የነበረ፤ የጌታውን ደርግ ጋዜጣ አዘጋጅና የኢሰፓ ተጠሪ ሆኖ የሰራ ነው ።

ለሻዕቢያ ወያኔ ያደሩም ድረ ገጾች ባለቤቶችም አሉ ።

ነፍሰ ገዳዩ ፍስሃ ደስታም አሁን ብቅ እያለ ነው ።

የተቃዋሚ ድርጅት መሪ ነኝ የሚልም ቀይ ሽብርተኛ ኢሕአፓን ያጠቃል ።

የደርጎች ብቅ ብቅ ማለት እየታየ ነው ። የአረመኔው መንግስቱ የደም ብዕር ውጤት ለህትመት ሲበቃ (ይህው አታሚ ሁለተኛውን ቅጽ ለማውጣት ደፋ ቀና ብሎ አምባገነኑ ወግድ ብሎታል) ፤ በነፍሰገዳዩ ፍቅረስላሴ የውሸት ጥራዝ ሲታጀብ የአረመኔው አገዛዝ ቁንጮዎች ጸሀያችን ወጣች አይነት ጉሬት መጀመራቸው በአደባባይ እየታየ ነው ። መድረክ አጣበዋል ። ኢሳያስ ኢትዮጵያን ይወዳል ይሉናል ። ኢሕአፓ ጸረአማራ ነበር፤ብዙዎችንም ጨረሰ ወዘተ ብለው ይጮሁብናል ። የገማ የገለማ ውሸቶችን እያደሱ ለአዲስ ትውልድ ሊግቱም ጥረዋል ። ፍስሓ ደስታ በጻፈው ለምሳሌ በዓለም የሰራተኞች ቀን በየቀበሌው የደርግ ታጣቂዎች ከሺ ያላነሱ ሰላማዊ ወጣቶች የገደሉትን አምኖ ይቅርታ በመጠየቅ ፈንታ

ለወንጀል ተጠያቂ ተገዳዩን ኢሕአፓ ሊያደርግ ሞክሯል ። ሌሎች አያሌ ክሶችን በራሱ ላይ ሳይሆን በድርጅቱ ላይ ደርድሯል ። ሀቁ ሲፈተሽ ግን እርምጃ ውሰዱ ብሎ በብዙ ሰነዶች ላይ ፊርማው የሚገኘው የዚሁ አውሬ ኮለኔል ነው ። ለወያኔ መሳሪያ ያቀበለውና በትግራይ የነበረውን ጦር ወያኔን ተወት አድርጋችሁ ኢሕአፓ/ሠ ን አጥቁ ብሎ ትዕዛዝ የሰጠው ፍስሃ ደስታ ነው ። ከአንዴም ሁለቴም ደርግን ከድቼ ለትግራይ ልታገል ፍቀዱልኝ ብሎ የወያኔ መሪዎችን የለመነውም ይህ ጉድ ነው ። ፍስሀ ደስታ በዘረኛነትና በህዝብ ማጥፋት ወንጀል ከነጓደኞች ለፍርድ መቅረብ ያለበት እንጂ መጽሃፍ ጽፎ ወንጀሉን ሲቀጥል በዝምታ የሚታይም ባልሆነ ነበር ። ይባስ ብሎ ግን ዛፎች የራሳችን ጠማማ እንዲሉ ከነበርን ስኳድ አንድ አባል የሆነ፤በታኝና አንጃ፤ ዓይኑን ሳያሽ የፍስሃደስታን ቅርሻት ውብ ብሎ ሌላ ወንጀለኛ ለሚመራው ራዲዮ ጣቢያ ቃለ መጠይቅ ሰጥቷል ። ከገሙ አይቀር ይግማሙ ይሏል ።

ወደ ለምን ስንመለስ እነዚህ የወደቀው አገዛዝ ማፈሪያ ቅሪቶች አንድ ወንጀላቸውን ለመደበቅ ሲሆን በድርጅቱ ላይ የሚዘምቱት በሌላ በኩል ደግሞ ሊያንሰራሩ ሲመኙ ጠላት ይሆነናል ብለው የሚፈሩትን ድርጅት ማጥቃት የሚል ዕቅድን በዋሺንግተን ከሚሰበሰቡበት ሬስቶራንት ውስጥ አውጠንጥነዋል ፡፤ ፍርሓት ነው ምንጩ፤ ወንጀልን ለማመን አለመፈለግ ነው ምንጩ ። ከዓመት ዓመት ራሱን እያጋለጠና በቅሌት አዳፍኔ የሚመታው ግለሰብ ለምሳሌ ለ60 የደርግ ሰለባዎች መገደል ምክንያት መሆኑንና ሊሎችንም ጥፋቱን ይህ ድርጅት ስለሚያውቅበት ሀ ብሎ ዋሾ አፉን ሲከፍት ኢሕአፓ ያ ትውልድ ብሎ ማውገዙ ቀንቶት ዓመታት አልፈዋል ። ይህ ታሪክ አበላሽና ሊሎችም ቢሆኑ ላለፉት ጓደኞቸው፤ላሉት መምህራቸው፤ለሚመጡ ነቢያቸው ሊሆኑ አይችልም፤ አልቻሉምም ። ያለፈውም ያለውም መጪውም ትውልድ የሚያወግዘው እንጂ ! ቆሻሻ ታሪክን ድበቃ፤ የነበረን የቡከን ህይወት ለመሸፈን፤ ደርጉ የሕዝብን አብዮት ድል ቀምቶ ስልጣን ሲይዝ ለሹመት ከአሜሪካ መመለስን ለማስረሳት፤ ለወያኔም ማደርን ለመሰወር የሚጥሩ ኡሉ ። ይህ የደም የመስዋዕትነት ሀውልት ሆኖ የቆየውን ድርጅት ማጥቃት ይፈልጋሉ ። አልጠፋ ያለው እሳት መጥፋት አለበት በሚል ቅዠት ናላቸውን ያዞራሉ ። ኢሕ አፓ ጠፍቷል ብለው ራሳቸውን ለማሳመን ያጓራሉ ። እሳቱን ለማጥፋትም የውሸት ጎርፍን ይለቃሉ ።ይህ ነው እየታየ ያለው ። እንደሚፈሩትና ሊፈሩትም እንደሚገባ የሚያውቀው ኢሕ አፓ ደርግ--ኢሠፓ ሲያንሰራራ እጁን አጣጥፎ የሚያይ አይደለምና ይታገላቸዋል ። ወንጀለኞቹንም ከዚህ በፊት ወያኔ ላይ በማተኮር ቸል ብሎት የነበረውን ትቶ የማጋለጡን ዘመቻ አጠናክሮ የሚቀጥልበት ይሆናል። በብሄረሰብ ድርጅቶች ጀርባ የሚደበቁትን ሳይቀሩ ርቃናቸውን ያስቀራል ።ይህ ሊያምኑት የሚገባ ቃል ነው ።

ሌሎች ደግሞ እንደ አቅሚቲ የየራሳቸውን ጣኦቶች ጠርበዋል። ከርቤና ብርጉድም እያጤሱ ናቸው ። ማንዴላ፤ሌዲ ሊበርቲ፤ ቆራጡ ፕሮፌሰር፤ አዋቂውና አስተማሪው ፕሮፌሰር ወዘተ እያሉ የሌላቸውን

ማንነት እያከናነቧቸው (ለባሾቹም ባያምርባቸውም በደስታ ተቀብለው) ቆጥ ያወጡና ትግሉን ሲበድሉ ቆሽ፤ረጋ በሉ፤ ያልሆነውን ሆነ አትበሉ፤ተክለ ሰውነትን ህልውና አትስጡ፤ለበሰ አሸበረቀ ያላችሁት ራቁቱን ነው፤ ግብዝነትን ብልህነት አታድርጉ ሲባሉ ወቃሹን ውጉዝ ከመ አርዮስ ወይም ቆሻሻ የነካ እንጨት ያደርጋሉ ። ኢሕ አፓ ጣኦት አንጠርብምም አናስጠርብምም በማለቱ ብዙ ችግር ደርሶበታል ። ከውስጡ ፈልተው ጣኦት በሉን ያሉትን ሲያሳፍራቸው ብተናና አንጃነትን አቀንቅነው ሊጎዱት ሞክረዋል፤አሁንም አላቆሙም ። ከበስተውጪ ያሉትን ደግሞ አስመሳይ ታጋዮች፤ ፈሪዎች፤የወያኔና የባዕድም ቅጥረኞች ብሎ ስለተቸ (ያውም እንደነሱ በተራና ጸያፍ የባለጌ ስድብ ሳይሆን በለሆሳስ፤በስነ ሥርዓት) እንዳበደ ውሻ ቦጫቂ ጥርሳቸውን ሰደውበታል ። ጣኦት ጠረባና ሀገር አድን ትግል አብረው ሊሄዱ የማይችሉ በመሆናቸው፤የጉልበት በሽተኛን ዳገት ውጣ ማለቱ ስህተት በመሆኑ፤ ባሩድ ሳይሸተው የሚፈረጥጠውን የጦር መሪ ለማድረግ መነሳት በራስ ላይ ጉዳት ማምጣት በመሆኑም የስህተት እርምጃና ተክለሰውነት ግንባታን ድርጅቱ ተቃውሟል ፤ ወደፊትም ይቃወማል ። ወደ ኋላ መለስ ብለን ጣኦት የተጠረበላቸውና ኢሕአፓ የተቻቸው መሪና አዋቂ ተብዬዎች ዛሬ የት ናቸው ብለን ብንመረምር ድርጅቱ የወሰደው አቅዋምና የሰጠው ማሳሰቢያ ትክክል መሆኑን እንገነዘባለን ። ኢሕአፓ ሶስት ጨቋኝና አውሬ አገዛዞችን ሳይፈራና ግንባሩን ሳያጥፍ የታገለ በመሆኑ በከንቱ ነጋ ጠባ የሚንጫጩበትን የታሪክ አተላዎችና ነፍሰ ገዳዮች ሊፈራ አይጠበቅም ። ተስፋ ያልቆረጠ መነኩሴ ምናኔ ሲሄድ ሴቲቱን ይሰናበታል የሚባልባቸው ናቸውና ይንቃቸዋል ። ተንኮለኛን አርቀህ ቅበረው ነውና ግን ሁሌም በዝምታ አያልፋቸውም ።

በኢሕአፓ ላይ ዋናው አዝማች ወያኔ ነው ። ይህ ለወያኔ አዲስ አይደለም --ገና በናቅፋ ሲመሰረት የጀመረው ነው ::እስካዛሬም የሚቀጥለው አሁንም ኢሕአፓ ጠላቱ በመሆኑ ነው ። ድርጅቱም በኩራት ጸረ ወያኔ መሆኑን ያምናልና በዚህ ላይ የሚደረግ እሰጥ አገባ የለም ። ወያኔ ገና ሲመሰረት ትግራይን የመገንጠል መርህ ግብር ይዞ ሲነሳና የሸዋ አማራን ሰይጣንነት ሲያሰማን ኢሕአፓ ተቃውሞታል ። ዛሬ ጸረ ወያኔን ነን ብለው የሚሉ ግን ወያኔ ትግራይ ምሽት ብሎ ሲነሳ በተለይ በአሜሪካ ገንዝብ አዋጪ እንደነበሩ አንዘነጋም ።ወያኔ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ ሲፈርምና ሲያስተጋባ ኢሕአፓ ተቃውሞታል ። የዚህ ሀቅነት ግልጽ ሆኖ ሳለ፤የሚመለከታቸውና ያወገዙትም (አስመራ መቀሌ) ያመኑት ሆኖ ሳለ በምኒሊክ ጊዜ የደነቆረ..እንዲሉ ደርግ የጋታቸውን ጸረ ኢሕአፓ ሀሰት ሁሉ ዛሬም የሚተፉና ድርጅቱ ኤርትራን ደገፈ፤የሻዕቢያም ነበር፤ወዘተ ብለው የሚቀጥፉ ማዘኛዎች አሉ ። ወያኔ

ኢሕአፓን በአማራ ትምክህተኛነት ሳይውል ሳያድር ከሶ፤አባይ ኢትዮጵያ የሚል ቅጽል ለጥፎለት ሊታገለው ተነሳ እንጂ፤ ሻዕቢያም ኢሕአፓ ኤርትራ ቅኝ ግዛት ናት አልል አለኝ ብሎ ሊያጠፋ/ሊያስጠፋ (በተለይ በርካታ ኤርትራውያን በድርጅቱ መሰለፋቸውን ጠልቶ ስለነበር) ተነሳ ጣረ እንጂ፤ ዚያድ ባሬም ቢሆን የኢሕ አፓ አባላት ከኦጋዴን መመልመላቸውን ተቃውሞና ድርጅቱ ምዕራብ ሶማሊያ የሚባለውን አላውቅልህም ስላለው ተነሳበት አጠቃው እንጂ ሁሉም ድጋፍ የሰጡት አልነበረም :: ይህን ሀቅ ለመደበቅ ደርግም ወያኔም ዛሬም ሲፍጨረጨሩ መታዘባችን አልቀረም ። ወያኔ ጸረ አማራ ብሎ ያወገዘውንና ስንቱን ሺ አማራ ተወላጅ በኢትዮጵያዊ ሰንደቅ አሰልፎ ያታገለውን ድርጅት ዛሬ ጸረ አማራ ብለው ሊያወግዙት የሚጥሩ መኖራቸው ምጸትና ቀቢጸ ተስፋነትን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል ። ቅጥፈትና ራስን ማዋረድ ሲነግስ ምን ይሏል!

ወያኔ ከአንዳንዶቹ ውድቀች የሚሻለው የራሱን ውሸት ራሱ የማያምን በመሆኑ ነው ። እሳቱ ጠፋ ሲል ብዙ ጊዜ ቢደመጥም ፤ የድርጅቱን ስም አላነሳም ብሎ ቢምልም ወደደም ጠላም ግን እሳቱ ተዳፈነ እንጂ እልጠፋም የሚለውን ያምንበታል ። ፍርሃቱም ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው ። በእጁ የወደቁትን የኢሕ አፓ መሪዎችና የቆዩ አባላትን አለፍርድ የረሸነውም ለዚሁ ነው (የደርግ ነፍሰ ገዳዮችን ተንከባክቦ ይዞ ባለበት !)። ወያኔ ኢሕአፓን አይፈራም የሚሉ ብዙዎች አይደሉም። ነጋ ጠባ ኢሕ አፓ ጠፍቷል፤ በተለጣፊው የዘቀጠ ቡድን ተተክቷል ብሎ ሕዝብን ለማሳመን የሚጥረው ስጋት ስላለው ነው ። በተለይ ከቅርብ ጊዘ ወዲህ የወያኔ ውስጣዊ ቀውስ እየተባባሰ በመሄዱና አንዳንድ የውጭ መንግስታት ድርጅቱን ጠጋ ብለውታል የሚል ማንም ያላረጋገጠው መረጃ ደርሶኛል ባይ በመሆኑ መርበትበቱ ጨምሯል ። ለቅጥረኞች በጸረ ኢሕአፓ ዘመቻ ጠንከር ብለው እንዲገፉ ያዘዘ ሲሆን መረጃ የሚለውንና ድርጅቱና መሪዎቹን ያስጠቃል የሚለውንም ዘርዝሮ አሸክሟቸዋል :: በድርጅቱ መሪዎች ላይ የተከፈተውን ለከት አልባ የስም ማጥፋት ዘመቻ ያጤናል ። አሁንም ቢሆን ወያኔ የሚያውቀውና የሚያምነው ሀቅ ብዙሃን ኢሕአፓን ደጋፊ መሆናቸውን ነው ። አሁንም ቢሆን ኢሕአፓ በህቡዕ አደራጅቶ ቀውስ ሊከተኝ ይችላል፤ችሎታም አለው ብሎ ማመኑም የሚደበቅ አይደለም ። ለዚህም ነው ጠፋ እያለ የለም አለ ብሎ ራሱን የሚቃረነው ። ለሌለ ድርጅት ይህ ሁሉ ጭንቀት፤ውግዘት፤ቅጥረኛ ምሁሮችን አሰማርቶ ተኗል ለማስባል መጣር ባላስፈለገ ነበር ።

ኢሕአፓ አለ፡፤ ተከፋፈለ ደከመ ያሉት ለቀጣይ ሀፍረት ተዳርገዋል ። እነ እገሌን ከአመራሩ አባረርን እስከማለትም ደርሰው ነበር ። ፍኖተን አል ሲሲን ለምነው አሳፈኑና አረፍንም ብለው ነበር ። ከንቱ ልፋት መሆኑን ሳይውል ሳይድር መገንዘብ ግን ተገደዱ ።የፍኖተ ዴሞክራሲ በሰፊው መደመጥና የሚያካሂደው ቅስቀሳ የራስ ምታትም ሆኖባቸዋል ። ይህም ነው ሌላኛው ምክንያት ለጸረ ኢሕአፓው

ዘመቻ መጧጧፍ ።ድርጅቱ እንቅስቃሴው በህቡዕ በመሆኑ ስፋት ጥንካሬው የሚታወቅ ባይሆንም ዳገቱን መውጣት ከጀመረ ግን ቢያንስ 24 ዓመታት ማሳለፉ የሚካድ አይደለም ። ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ጀምሮ በትጥቅ ትግልም ይህን ጉድ ከኢትዮጵያ ለማስወገድ ዝግጅቱን ቀጠለ አጧጧፈ እንጂ ከወያኔ አልተለጠፈም፤በወያኔ አልተሾመም፤ሰላማዊ ህጋዊ እያለ ራሱንም ሕዝብንም አላደናገረም ። ለኢአግ ምሰረታና ትግልም መሰረት ሆኖ መስዋዕትነትን ከፍሏል ። ትግል ሲል ግን የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም በማስቀደምና በራሱ ወሳኝነት ነውና ከማንም ተለጥፎ ወይም ለኢትዮጵያ ጠላቶች የመስገድ አማራጭን አልወሰደም፤ሊወስድም ይዘቱ እስከዛሬም አልፈቀደለትም ። እስቲ አፉን ሞልቶ ይህን የሚል ድርጅት ብቅ ይበልና እንስማው !

የኢሕአፓ ህልውና እንደ ኤልቪስና ቱፓክ ሞተ አለ ክርክር የሚገባበት አይደለም ። የወያኔና መሰሎቹ ጫጫታ ራሱ በቂ ምስክር ነው ። አንዳንዶች በፖለቲካው መስክ ምሁር በሉን ቢሉም መሃይም ናቸውና የድርጅቱን ረጅም ዓመታት ህልውና እንደ መርገም ሊያቀርቡ ሲጥሩ ይታያሉ ። ድርጅቱ ይህን ሁሉ ዓመታት፤ ያ ሁሉ ሽብርና ጥቃት ደርሶበት፤ ይህ ነው የማይባል ዘመቻን ችሎ፤ክህደትን ተቋቁሞ፤የሰርጎ ገቦችን ጥቃት መክቶ አሁንም ህልው ሆኖ መቀጠሉ የሚያስመሰግነው ነው ። ስንቱ ድርጅት በሉኝ ባይ በተመሰረተ በአጭር ዓመታት የሚጠበቀውን የ 15 ደቂቃ ዝናን ካገኘ በኋላ ከሰመ ? አለን ብለው ቀፎ የሆኑ ቡድኖች አሉ ። ከቁጥር የማይገቡ ። ኢሕአፓ ግን አለሁ ሲል አፋዊ ሳይሆን መዋቅሩንና ግዳጁን ጠብቆና ባለው አቅምም እየተንቀሳቀሰ ነው ። ህልውናው ደግሞ ለመኖር ምክንያት ስታጣ ሌሎችን ለማበሳጨት ኑር በሚል ሳይሆን (ማበሳጨቱም አስመስጋኝ ነው) ሲመሰረት የገባውን ቃል ኪዳን ለማክበርና ትግሉንም ከግብ ለማድረስ ነው ። የተዋቀረ፤ሙያተኛ አሰራን የሚያውቅና ሊያስተምር የሚችል፤ከትምክህትም ሆነ ጠባብነት መራቅ ያመነበት የሆነ፤ በጉባኤዎችና ስብሰባዎች ራሱን የሚገመግምና ቃል ኪዳኑን የሚያድስ፤ በውጭ ሀገራት ቢሮዎች ከፍቶ የሚሰራ፤ ለዓመታትም ወደ ሀገር የሚያስተላልፍ ራዲዮ በራሱና በአባሎቹ ጥረት የሚያካሂድ ድርጅት ነው ። ከሁሉም በላይ ግን ድርጅታዊ ጥቅምን በገፍ ሊያገኝ እየቻለ የሀገርን ጥቅማን ሉዓላዊነት መቸም ቢሆን መቼ አሳልፎ ያልሰጠ ነው ። እስቲ ሌሎች ይህን ያህል ታገልን፤ ለማንም ሳንሰግድ ኢትዮጵያን አስቀድመንና ሉዓላዊነቷን አክብረን ይበሉ!

ኢሕአፓ ዓላማው ድብቅ አልነበረም፤ መፈክሮቹ ግልጽና ሕዝባዊ በመሆናቸ የሕዝብን ሙሉ ድጋፍ አግኝቷል ። ኢሕአፓን በትዝታ መልክ ማቅረብ የሚፈልጉም ቢያንስ የኩራትና የደስታ፤የቆራጥነትና ጀግንነት ትዝታ መሆኑ አያጠራጥርም ።መሬት ለአራሹ፤ስልጣን ለጭቁኑ ሕዝብ፤ዴሞክራሢ ለሰፊው ሕዝብ፤ሉዓላዊነት ለኢትዮጵያ፤ የሕዝብ እኩልነት ይረጋገጥ ፤ብሄራዊ ኤኮኖሚ ይገንባ ወዘተ በሚል

ታገለ እንጂ የማንንም የግል ሆነ የብዙ አምባገነን ስርዓትለማምጣት ደሙን አላፈሰሰም። በከሸፈ ፕሮፌርሰር በሉን ባይ አጋፋሪነት ድርጅቱ ለስልጣን ታገለ ብለው በክስ መልክ ለሚውገረገሩ ትላንትም ዛሬም መልሱ ታዲያ የማንን ጎፈሬ ለማበጠር ነበር የሚል ይሆናል ። ትግል ለስልጣን ነው።ከጨቋኞች ቀምቶ ሕዝብን ወሳኝና ፈላጭ ቆራጭ ለማድረግ ። ኢሕአፓ ለግል ስልጣን ቢቋምጥ ኖሮማ ከመጣው ጋር እየተሞዳሞደ፤እንደ ሌሎቹ ለባዕዳን እያደረ የሆነች ስልጣንም ባለቤት ሆኖ በሕዝብ ላይ በተጫነ ነበር ። በኢትዮጵያ ለሀገርና ለህዝብ ብሎ ያካሄደውን ክቡር ትግል ታሪክ ይመስክርለታል ። ከወያኔ ጋር በብሄር ጥያቄ፤በኢርትራ ጥያቄ፤ በዲሞክራሲ ጥያቂ ያካሄደውም ትግል በጽሁፍ የሰፈረ ነው ። የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን ምንነቱን ብቻ ሳይሆ ቃሉንም ለወያኔ ያስተማረው ኢሕአፓ ነው ። ማለትም በጸረ ወያኔው ትግል ከተሰማራ ብዙ ብዙ ዓመት አልፏል ። ለአማራውም ለሌላውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ተቆርቋሪነቱ ደርግ ሲወድቅ ወይም ከ1997 ምርጫ በኋላ የጀመረ አይደለም ። ድህነት ወንጀል አይደለም፤ ገባርነት ያብቃ፤ መብት ይከበር፤የሴቶችና የህጻናት መብት ይከበር፤ ሙስሊሞች አይበደሉ፤ ነጻ ትምህርት ለሁሉምና መሰል መፈክሮች የአንድ ክፍል ብቻ አልነበሩም ። ተራማጅ ወጣቶችስ ረሀብን በማጋለጥ የነበራቸው ሚና የሚካድ ነው ? ላባደርና ሰርቶ አደር ስንልም ማንንም ሕዝብ የሚያገል አልነበረም ። ካላወቁ አይነቁ ነውና እየተነገረ አልሰማ ማለት ራስን የሚያስገምት ነው ።

እየነገርናቸው እያረጉት ዋዛ

ቅሌትን አፍቅረው ውሸታቸው በዛ

ማለቱን ብናቆም ምንኛ ደስ ባለን ነበር !

ይቀጥላል !